# ለልብ ህሙማን ህጻናት እንድረስላቸው!!

ብዙዎቻችን የልብ ህመምተኛ ልጅ ቢኖረንና አክመው ሊያድኑት የሚችሉት ባላሙያዎች በውጭ ሀገር እንዳሉ እያወቅን ነገር ግን ለህክምና የሚጠይቀው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት የልጃችን የወደፊት ተስፋ ሲጨልም እንኳን ማየቱ ይቅርና ማሰቡም ይከብደናል።

## በኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ህጻናት መርጃ (በኢልህህመ) ምንድን ነው?

የልብ ህሙማን ህጻናትን ለመርዳት በቆሙ በጎ ፈቃደኞች የተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነና ለትርፍ ያልቆመ ድርጅትነው። የኢትዮጵያ ፍትህ ብሄር ቁጥር 321/59 በሚፈቅደው መሰረት ተመዝግቦ ህጋዊ ሰውነት አግኝቷል።

## በኢልህህመን ማቋቋም ለምን አስፈለገ?

- የልብ ህመም ህጻናትን በብዛት እያጠቃ መሆኑን በመገንዘብ፣
- በሀገራችን የልብ ህመም ህክምና በተለይም የልብ ቀዶ ህክምና ተቋም አለመኖሩን በመረዳት፣
- ለልብ ህመም የሚደረገው ህክምና በየትኛውም ቦታ ውድ መሆኑንና ከአብዛኛው ሰው አቅም በላይ መሆኑን በመረዳት፣
- ሌሎች ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚችሉ አሳሳቢ በሆኑ ችግሮች የተነሳ የልብ ህሙማንን ለማከም የሚያስችል የወደፊት ተሰፋ ባለመታየቱ፣

## የበኢልህህመ ኣላማዎች ምንድን ናቸው?

- የልብ ህሙማን ህጻናትን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ተገቢውን ህክምና እንዲያገኙ መርዳት፣
- ህዝቡ ሰለ ህጻናት የልብ ህመም ተረድቶ መከላከል እንዲችል ግንዛቤ መፍጠር፣
- የልብ ህመምተኛ ህጻናትን ተቋም ማቋቋምና በመሳሪያ ማደራጀት።

## በኢልህህመ ከየት ወዴት?

በኢልህህመ ከተጤጤመበት ከ1981 ኣ.ም. ጀምሮ ከ1200 በላይ የልብ ህሙማን ህጻናትን በእስራኤል፣ በኔዘርላንድ፣ በእንግሊዝ፣ በአሜሪካ፣ በጣሊያን፣ በሰዊዘርላንድ፣ በጀርመን፣ በግሪክና በኢትዮጵያ የልብ ቀዶ ህክምና እንዲያገኙ አድርጉል።

የረዝም ጊዜ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ከ1996ኣ.ም. ጀምሮ ደግሞ በጥቁር አንበሳ ሆሰፒታል ግቢ የልብ ህክምና ማእከል በመግንባት ላይ ይገኛል።

የግንባታው ወጭ 12 ሚሊዮን ብር የሚገመት ሲሆን በጥቅምት 1999 ዓ.ም. ተጠናቆ ጥር 1999 ዓ.ም. ስራውን ይጀምራል ተብሎ ይገመታል።

ማእከሉ ስራውን ሲጀምር በልብ ህመም የሚሰቃዩ ህጻናትን ነጻ ህክምና ሲያገኙ ሆሰፒታሉ ከሚኖሩት አልጋዎች 10% ለአዋቂዎች ይውላል።

ከ 96 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የልብ ህክምና መሳሪያዎ ከውጭ አገር በእርዳታ የሚገኙ ሲሆን ማእከሉ ህክምና ከመሰጠት ጎን ለጎን የስልጠናና የምርምር ማእከል ይኖረዋል።

የልብ ህክምና ማእከሉ ግንባታ የሚከናወነው መንግሰታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከበጎ አድራጊ ግለሰቦች በሚገኝ እርዳታ ነው።

---

## THE PAST AND THE FUTURE

Since its establishment in 1989, CHFE helped more than 1200 children with heart defects. The surgical treatment of these patients took place in Israel, The Netherlands, Germany, USA, Italy, Switzerland, United Kingdom, Greece and Ethiopia: in the later by visiting surgical teams.

In the last two years (Since 2004), CHFE has embarked upon its long-term objective the construction of a Cardiac Center in the premises of the Black Lion Hospital. The total cost of the building is estimated to be 12 million Birr and construction is scheduled to be completed in October 2006 with the hope of commissioning it by January 2007. Equipment needed to run the hospital, costing over 90 million Birr, is expected from our international benefactors, CHFE intends to allocate at least,10% of its bed capacity for adult services.

The cost of construction of the center to date has been shouldered by the generous contributions of concerned individuals and agencies and we are forever grateful. However, we have a long way to go and **WE NEED MORE MONEY to finish the building**. Ethiopia, a country of over seventy million does not have a single cardiac center. We deserve better!! We would like to call upon fellow Ethiopians both at home and overseas to join hands and help us realize this dream of ours.